

# +++ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ +++

# የዕለት እንጀራ

የፍልሰታ ጾም - ፲፮ኛ ቀን [፪፻፹፫ኛው እንጀራ] ነሐሴ ፲፮ ፳፻፮



**እንኳን ለዛሬው ነሐሴ ፲፮ የእመቤታችን የትንሣኤና ዕርገት በዓል አደረሳችሁ ፡፡**

አቤቱ፥ ወደ ዕረፍትህ ተነሥ፥ አንተና የመቅደስህ ታቦት።

መዝሙር ፻፴፩፡፰

ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ ፥ ወይስ ጭንቀት ፥ ወይስ ስደት ፥ ወይስ ራብ ፥ ወይስ ራቁትነት ፥ ወይስ ፍርሃት ፥ ወይስ ሰይፍ ነውን?

ስለ አንተ ቀኑን ሁሉ እንገደላለን ፥ እንደሚታረዱ በጎች ተቆጠርን ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው።

በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።

ሞት ቢሆን ፥ ሕይወትም ቢሆን ፥ መላእክትም ቢሆኑ ፥ ግዛትም ቢሆን ፥ ያለውም ቢሆን ፥ የሚመጣውም ቢሆን ፥ ኃይላትም ቢሆኑ ፥ ከፍታም ቢሆን ፥ ዝቅታም ቢሆን ፥ ልዩ ፍጥረትም ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ።

ሮሜ ፰፡፴፭-፴፱

እግዚአብሔር ታላቅ ነገርን አደረገልን፥ ደስም አለን።

መዝሙር ፻፳፭፡፫

## በዚህ ቀን ከሚታሰቡት መካከል

የእመቤታችን ትንሣኤና ዕርገት

### የዕለቱ ምስባክ ፡

ቀደሰ ማኅደሮ ልዑል
እግዚአብሔር ውስተ ማዕከላ ኢትትሐወክ
ወይረድአ እግዚአብሔር ፍጽመ

መዝሙር ፵፭፡፬-፭

### ትርጉም ፡

ልዑል ማደሪያውን ቀደሰ።
እግዚአብሔር በመካከልዋ ነው አትናወጥም፥
እግዚአብሔርም ፈጥኖ ይረዳታል።